**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ז, 2017

**מספר השאלון: 022284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה

## לעולים חדשים

## על פי תכנית הרפורמה ללמידה משמעותית

**הוראות לנבחן**

א. משך הבחינה: שעתיים וחצי.

ב. מבנה השאלון ומפתח ההערכה:

בשאלון זה ארבעה פרקים. ענה על שאלה אחת מכל פרק.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק שני | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק שלישי | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| פרק רביעי | — | (25x1) | — | 25 נקודות |
| סה"כ | | | — | 100 נקודות |

**שים לב:** תלמידים **שאושר להם מבחן מותאם** יענו על שלוש שאלות: שאלה אחת מפרק ראשון **או** מפרק שני, שאלה אחת מפרק שלישי ושאלה אחת מפרק רביעי.

ג. חומר עזר מותר בשימוש:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

כתוב במחברת הבחינה בלבד, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב כטיוטה (ראשי פרקים, חישובים וכדומה). רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים שמחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦

የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ወቅት: የ2017 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 022284**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

## በሪፎርሙ ትርጉም ያለው የማስተማር ዕቅድ መሠረት

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

ኦ. ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ፦

ይህ ፈተና አራት ምዕራፎችን ይዟል። ከእያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ ጥያቄ መልስ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሦስት | — | (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| ምዕራፍ አራት | — | (1x25) | — | 25 ነጥብ |
| | | በአጠቃላይ | — | 100 ነጥብ |

**ልብ በል፦ ተስማሚ ፈተና** (מבחן מותאם)

**የተፈቀደላቸው** ተማሪዎች ሦስት ጥያቄዎችን ይመልሱ፦ ከምዕራፍ አንድ **ወይም** ከምዕራፍ ሁለት አንድ ጥያቄ፣ ከምዕራፍ ሦስት አንድ ጥያቄ እና ከምዕራፍ አራት አንድ ጥያቄ።

ג. ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

እንደ ንድፍ (טיוטה) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ።
በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ።
ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ቅሉ ለሴትም ለወንድም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (25 ነጥብ)

**የመጀመሪያው ወቅት፦ ብሔርተኝነት በእስራኤልና በሕዝቦች ዘንድ - ከጅማሬው እስከ 1920**

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**1. ዘመናዊው ብሔርተኝነት**

**ሀ.** ለአንድ ብሔር ትውልድ የጋራ መለያዎች ምንድን ናቸው?
በአውሮፓ ውስጥ በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የብሔርተኝነት እንቅስቃሴን አንድ ዓላማ አብራራ። (12 ነጥብ)

**ለ.** የኢንዱስትሪው አብዮት (המהפכה התעשייתית) በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በብሔርተኝነት እንቅስቃሴ እድገት ላይ ያደረገውን ተፅዕኖ አብራራ።
በዚህ ወቅት ለብሔርተኝነቱ እንቅስቃሴ እድገት አንድ ተጨማሪ መንስዔ አቅርብ። (13 ነጥብ)

**2. የባሰል እቅድ፣ የኡጋንዳ እቅድ**

**ሀ.** የባሰል እቅድ (ዓላማና መገልገያው) ምን ነበር? አስፈላጊነቱስ ምን ነበር? (12 ነጥብ)

**ለ.** የ"ኡጋንዳን እቅድ" ሐሳብ ያቀረበው ማን እንደሆነ እና ይዘቱ ምን እንደነበር ጻፍ።
የኡጋንዳን እቅድ አንድ የሚደግፍ ማሳመኛ ሐሳብ እና አንድ የሚቃወም ማሳመኛ ሐሳብ አቅርብ። (13 ነጥብ)

**3. ምድረ እስራኤል ከ1882–1914 ባሉት ዓመታት**

**ሀ.** ከ1882-1914 ባሉት ዓመታት በምድረ እስራኤል ላይ የተቋቋሙ ሁለት የአሰፋፈር ቅርጾችን አቅርብ እና በእነዚህ ዓመታት ለነበሩ አዲስ ገቢዎች ላይ የነበሩትን ችግሮች አብራራ። (13 ነጥብ)

**ለ.** ከ1882-1914 ባሉት ዓመታት አዲስ ገቢዎች በባሕል እና በትምህርት ዘርፍ ያደረጓቸውን ሁለት እንቅስቃሴዎች አሳይ እና የእነዚህን እንቅስቃሴዎች አስፈላጊነት አብራራ። (12 ነጥብ)

ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ ሁለት (25 ነጥብ)

### ሁለተኛው ወቅት፦ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል (ከ1920-1939)፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የይሁዳውያን ሠፈራ በእስራኤል አገር

ከ4-6 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**4. "የዊልሰን 14 ነጥቦች" ፣ የማንዴቱ ዘዴ**

ሀ. ከ"ዊልሰን 14 ነጥቦች" ሰነድ ውስጥ ሦስት ንዑሳን አንቀጾች አቅርብ እና ከሰነዱ ንዑሳን አንቀጾች ውስጥ አንዱ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ ፖለቲካዊ ካርታ ላይ እንዴት እንደተገለጸ/እንደተተገበረ አሳይ። (16 ነጥብ)

ለ. የማንዴቱ ዘዴ ምን እንደሆነ አብራራ። (9 ነጥብ)

**5. በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል የይሁዳዊያን ሠፈራ በእስራኤል ሀገር**

ሀ. በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል ወደ እስራኤል አገር የመጡትን አዲስ ገቢዎች መለያዎች አቅርብ እና ከመለያዎቹ ውስጥ አንዱ በዚህ ወቅት ከተቋቋሙት ወይም ከተመሠረቱት የሠፈራ ዓይነቶች/ቅርጾች ውስጥ በአንዱ እንዴት እንደተገለጸ አብራራ። (15 ነጥብ)

ለ. "የእስራኤል አገር የዕብራዊያን ሠራተኞች አጠቃላይ ፌዴሬሽን" ("ההסתדרות הכללית של העובדים העבריים בארץ־ישראל") (1920) ለምን ተቋቋመ? የዚህን ፌዴሬሽን ሁለት የእንቅስቃሴ መስኮች አቅርብ። (10 ነጥብ)

**6. በአሥራዘጠኝ ሰላሳዎቹ ዓመታት ይሁዳዊያን፣ አረቦች፣ ብሪታንያዊያን በእስራኤል ሀገር**

ሀ. በአሥራዘጠኝ ሰላሳዎቹ ዓመታት የይሁዳዊያን ሠፈራ የደህንነት ዘርፍ/መስክ ዝግጅቱን ለማጠናከር ምን እንዳነሳሳው አብራራ እና በዚህ ዘርፍ/መስክ ከተደረጉት እንቅስቃሴዎች ሁለቱን አቅርብ። (13 ነጥብ)

ለ. የሦስተኛውን "ነጭ መጽሐፍ" (1939) ዋነኛ ይዘት አቅርብ እና ለዚህ መጽሐፍ መውጣት (פרסום) አንድ መንስዔ አብራራ። (12 ነጥብ)

ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ ሦስት (25 ነጥብ)

### ሦስተኛው ወቅት፦ አምባገነኑ መንግሥት (המשטר הטוטליטרי) ፣ ናዚነት፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የይሁዳውያን መጨፍጨፍ (השואה)

ከ7-10 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**7. የናዚ መንግሥት በጀርመን (1933-1939)**

ሀ. "የረጃጅሞቹ ቢላዋዎች ሌሊት" (ליל הסכינים הארוכות) ወይም የማረጋገጥ ሕግ/ተግባር (חוק ההסמכה) ውስጥ አንዱን እርምጃ አቅርብ። ያቀረብከው እርምጃ በናዚ ርዕዮተ-ዓለም (אידאולוגיה) "የመሪ መመሪያ ሕግ" ("עקרון המנהיג")ን ለማጠናከር እንዴት እንዳገዘ አብራራ። (12 ነጥብ)

ለ. በጀርመን ውስጥ ጀርመኖችን እና ይሁዳዊያንን ለማለያየት የናዚ አገዛዝ የወሰደውን አንድ እርምጃ አቅርብ እና ይህ እርምጃ ያጠናከረውን የናዚ ዋና ርዕዮተ ዓለም አብራራ። (13 ነጥብ)

**8. ማጎሪያዎቹ (הגטאות)**

ሀ. ናዚዎቹ ማጎሪያዎቹን ያቋቋሙባቸውን ዓላማዎች አብራራ እና ከዓላማዎቹ ውስጥ አንዱን ለማስፋፋት ሲባል ናዚዎች ካደረጓቸው እንቅስቃሴዎች ሁለቱን አቅርብ። (15 ነጥብ)

ለ. የ"መጨረሻው መፍትሔ" ("הפתרון הסופי") እስኪፈጸም ድረስ ከማጎሪያው የወጣቶች እንቅስቃሴ ድርጊቶች ውስጥ ሁለቱን አቅርብ። እነዚህ የወጣቶች እንቅስቃሴ ለአባላቱ የማጎሪያውን ሕይወት ይቋቋሙት ዘንድ እንዴት እንደረዷቸው አብራራ። (10 ነጥብ)

**9. ናዚዎችን መቃወም (ההתנגדות לנאצים)**

ሀ. በናዚ ወረራ ሥር በነበሩ ሀገሮች የነበሩት ይሁዳዊያን ያልሆኑ ሰዎች ይሁዳዊያንን ለመርዳት ያነሳሷቸውን ሁለት ምክንያቶች አብራራ።
ይሁዳዊያንን ለመርዳት የተጠቀሙባቸውን ሁለት መንገዶች አቅርብ። (13 ነጥብ)

ለ. የማጎሪያው አማጺያንን ዓላማዎች አቅርብ እና የዋርሶን ማጎሪያ አመጽ/ተቃውሞ ልዩ መሆን አብራራ። (12 ነጥብ)

**10. "የመጨረሻው መፍትሔ" ("הפתרון הסופי")**

ሀ. የይሁዳዊያን የጅምላ ግድያ/ጭፍጨፋ ጀርመኖች ወደ ሶቪየት ኅብረት ሰብረው ሲገቡ (ሶቪየት ኅብረት ስትወረር) በ(ሰኔ 1941) ለምን እንደጀመረ አብራራ። (13 ነጥብ)

ለ. በናዚ ወረራ ሥር በነበሩት ሃገራት የነበሩ ሰዎች ከናዚዎች ጋር የተባበሩባቸውን ምክንያቶች አብራራ። (12 ነጥብ)

ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ አራት (25 ነጥብ)

### አራተኛው ወቅት፦ እስራኤል ሀገርን በመካከለኛው ምስራቅ መገንባት

ከ11-14 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**11. የሀገረ-እስራኤል ጥያቄ - በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት**

ኦ. ብሪታንያ ሀገረ-እስራኤል የሚለውን ጥያቄ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንድታስተላለፍ ያደረጋትን አንድ መንስኤ አቅርብ እና ኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) የተወሰነውን የተባበሩት መንግሥታትን ዋና ውሳኔ አቅርብ። (15 ነጥብ)

ב. ኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 የተባበሩት መንግሥታት ድምጽ በሰጡበት ጊዜ የሶቪየት ኅብረት አቋም ምን ነበር?
በዚህ አቋም ላይ "ቀዝቃዛው ጦርነት" ያደረገውን ተጽዕኖ አብራራ። (10 ነጥብ)

**12. በ1950-ዎቹ እና በ1960-ዎቹ ዓመታት ወደ እስራኤል ሀገር መግባት (עלייה)**

ኦ. በ50ኛዎቹ እና 60ኛዎቹ ዓመታት ለአዲስ ገቢዎች ወደ እስራኤል ሀገር መግባት ሁለት ምክንያቶችን አብራራ፦ ከእስላም ሃገራት ወደ እስራኤል ለመምጣት አንድ ምክንያት እና ከአውሮፓ ወደ እስራኤል ለመምጣት አንድ ምክንያት። (10 ነጥብ)

ב. በ50ኛዎቹ እና 60ኛዎቹ ዓመታት በእስራኤል ሃገር ላይ በአዲስ ገቢዎች ላይ የነበሩትን ሦስት ችግሮች አቅርብ። ይህ የአዲስ ገቢዎች ወደ እስራኤል ሃገር መምጣት ሃገሪቱን እንዴት አጠናከራት? (15 ነጥብ)

**13. የ"ሾአ" መታሰቢያ (זיכרון השואה)**

ኦ. እስራኤል ሃገር ሾአን ለማስታወስ/ለማሰብ ከተጠቀመችባቸው መንገዶች ሁለቱን አቅርብ።
የሾአ መታሰቢያን አስፈላጊነት አብራራ። (15 ነጥብ)

ב. የእስራኤል ማህበረሰብ ከ"ሾአ" ጭፍጨፋ በተረፉት ላይ ላላቸው አመለካከት÷ የእስራኤል ጦርነቶች የሚያደርጉትን ተጽዕኖ አብራራ። (10 ነጥብ)

**14. የስድስቱ ቀን ጦርነት/ የአስተሰርዮ ጦርነት (מלחמת ששת הימים / מלחמת יום הכיפורים)**

ከሁለቱ ጦርነቶች አንዱን ምረጥ፦ የስድስቱ ቀን ጦርነት ወይም የአስተሰርዮ ጦርነት።

ኦ. የመረጥከው ጦርነት እንዲፈነዳ ያደረጉትን መንስኤዎች አብራራ። (13 ነጥብ)

ב. የመረጥከው ጦርነት በእስራኤል ሃገር ላይ ያደረገውን አንድ ተጽዕኖ እና በአረብ ሃገሮች ያደረገውን አንድ ተጽዕኖ አብራራ። (12 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך